# የ ኢትዮጵያ ሕፃናት ሕክምና ማህበር መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

የልጆች የአኗኗር ሁኔታ፣ ጥበቃ እና እድገት በአብዛኛው ከግብ ሊደርስ የሚችለው በጉዳዮ ላይ ግንዛቤ በዳበረ ህብረተሰብ፣ኃላፊነት በለባቸው የመንግስት አካላት እና ተነሳሽነት ባላቸውና በሚመለከታቸው ሙያተኞች ሲሆን በተለይም ይህንን ኃላፊነት ከግብ ለማድረስ ከፍተኛው ኃላፊነት የወደቀው በሕፃናት ሐኪሞች ላይ ነው፤ ምክንያቱም የሕፃናት ሐኪሞች ለሕፃናት የተሟላ ሕክምና መኖርና ሕጋዊ ጥበቃ መከበር ግንባር ቀደም ሆነው ኃላፊነቱን መሸከም ስለሚገባቸው ስለሆነም እኛ የኢትዮጵያ ሕፃናት ሐኪሞች (pediatricians) በሀገራችን የሚታየውን የህፃናት የጤና ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት በሚደረገው ጥረት የበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ያስችለን ዘንድ ይህንን የሕፃናት ሕክምና ማህበር አቋቁመናል።

## አንቀጽ 1፡ መቋቋም

<u>የኢትዮጵያ ሕፃናት ሕክምና ማህበር</u> በ_____________ ቀን በ______________ ዓ.ም. ተቋቁሟል።

## አንቀጽ 2፡ ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ይህ ማኀበር "<u>የኢትዮጵያ ሕፃናት ሕክምና ማህበር</u>" በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኃላ "ማኀበር" ተብሎ ይጠቀሳል።

## አንቀጽ 3፡ ዓላማ

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) የኢትዮጵያ ሕፃናት ሕክምና እንቅስቃሴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ጥረት ማድረግ፣

ለ) ከልጆች ጤና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የዕቅድና የአፈፃፀም ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣

ሐ) በህፃት ሕክምናና ጤና ላይ የምርምር ሥራዎችን መሥራት፣

መ) የማህበሩን አባላት ሙያዊ ፍላጐት ማሻሻል፣ መጠበቅ፣እንዲሁም በህፃናት ሕክምና ጥበቃና ምርምር ላይ ሥነ ምግባራዊ ሥራዎችን ማስፈን፤

## አንቀጽ 4፡ የበጀት ዓመት

የማህበሩ የበጀት አመት ከ ሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ይሆናል።

## አንቀጽ 5፡ ትርጉም

1. "ማህበር" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሕፃናት ሕክምና ማህበር ነው፡፡
2. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፡፡
3. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት ማስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰርት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡

## አንቀጽ 6፡ መደበኛ አባላት

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባአ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል፡፡
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የማየሟላ/የምታሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሰው መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች፡፡

   ሀ. ሕጋዊ ማረጋገጫ ያለው የሕፃናት ሀኪም/pediatrician/

   ለ. በማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን/የምታምን፤

   ሐ. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ- ምግባር ደንቦችን የማቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፣

   መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ሰምምነት የማደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል፣

   ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ች፣

## አንቀጽ 7፡ የክብር አባላት

1. የማህበሩ አባል ያልሆኑና የማህበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ ማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን የገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ፡፡
2. የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡

## አንቀጽ 8፡ የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው፣
2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው፡፡
3. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል፡-
   ሀ. ለማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፤
   ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ሰለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፤
   ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ሰብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው/አላት፡፡
   መ. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የመስማት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 9፡ የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም አባል የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ መክፈል አለበት/አለባት፣
2. አንድ አባል ከባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በት የማፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ መክፈል ይኖርባታል፣
3. ማንኛውም አባል የማህበሩን የመተዳደሪየ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባደ የሚወጡ መመሪያወችና ውሣኔዎችን ማክበር አለበት/አለባት፣
4. ማንኛውም አባል የማህበሩን ዓላማና የገባዡው/የገባችውን ግዴታዎች ማክበር፣ የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የማጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት/አለባት፡፡
5. በማህበሩ መደበኛ አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት፡፡

## አንቀጽ 10፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የማደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባዔው ይወሰናል፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል፡፡
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ለይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊየነሳ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የማቋረጠው፣

1. ሲሞት/ስትሞት
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም ሰሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
4. ለማህበሩ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸውም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት የህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤው ከባለነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣
6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤተ ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ቢወገድ/ስትወገድ፣
7. ከማህበሩ አባልነተ በራሱ/ሷ ፍቃድ ለመለቀቅ በጽሁፍ ሲጠየቅ/ስትጠየቅ ይሆናል፣

## አንቀጽ 12፡ የማህበሩ አደረጃጀት


1. ማህበሩ የማከተሉ የአማራር አካላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ

   ለ. ኦደተር

   ሐ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

   መ. ጽሕፈት ቤት፡፡
2. ማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው፡-




3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦደተር ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የማያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪየ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባአው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣
   - ለ. የማህበሩን መተዳደሪየ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   - ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን ይወስናል፣
   - መ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን፣የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል፣ ይሽረል፣
   - ሠ. የማህበሩን ዋና መስራያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   - ረ. ማህበሩን ማፍረስ ንበረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣
   - ሰ. የማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ህመታዊ በጀት ያፀድቃል፣
   - ሸ. ዓመታዊ የስራ ኘሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   - ቀ. በማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጀ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   - በ. የማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   - ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከባልነት እንዲሠረዝ ይወስናል፣
   - ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣
   - ኀ. የማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣
   - ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣
   - ኘ. ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመክፈል ወይም የመለወጥ የመጫረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
   - አ. በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ) ፣(በ) ፣(ቸ) እና (ኀ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜየዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላላፍ ይችላል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደራያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 14፡ የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገንቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ለይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ነው፡፡
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ  እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ባታል፡፡
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሳብ ያለው/ ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን/ቧን በቃል ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች፡፡
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለአጀንሲው ሊያለመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላላች፡፡

## አንቀጽ 15፡ የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የማኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. የጠቅላላ ጉባዔ ሰብሳቢ
   - ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሰባዎችን ይጠራል/ትጠራለተ ከፀሀፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል /ታዘጋጃለች፣
   - ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣
   - ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችን የሚሰጣቸውን ውሣኔዎችን በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ ትከታተላለች፣
   - መ. ጉባኤው ያጸድቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፣የሥራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃማዎችና ለለጋሾች እንደደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣
   - ሠ. ጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣
2. ምክትል ሰብሳቢ
   - ሀ. ሰብሳቢው/ዋ በማይህርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሠራለች፣
   - ለ.በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች የከናውናል፣
3. ፀሐፊ
   - ሀ. ከሰብሳቢ/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን የዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣
   - ለ የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ ትይዛች፣

## አንቀጽ 16፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ሰብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ሰብሰባ ያልጠራ እንደሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የማሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. የማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በፕሬዝዳንቱ ወይም ሊቀመንበሩ ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡
5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ቦታውን፣ቀኑን፣ ጊዜውን እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡
6. የማህበሩ አባለላት ከግማሽ በላይ ከተገኘ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
7. ከላይ በንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟለ የጠቅላላ ጉባኤዉ ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጎል/ ታደርጋለች፡፡
8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ ኘሬዝዳንቱ/ ለጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡

## አንቀጽ 17፡ የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ማህበህሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባዔው ምርጫ ሲየደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እነደ አስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ አንድ የምርጫ ዘመን /4 ዓመት/ መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
7. የማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ከማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፤ ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተማራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሰራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱበት ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳነት ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡት ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

## አንቀጽ 18፡ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት

1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ሆኖ የማህበሩን የእለት ተእለት ሥራ ያከናውናል፡፡
2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡፡
   ሀ. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲጸድቅ ይደርጋል፣
   ለ. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ መርሀ-ግብርና የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲጸድቅ የደርጋል፣
   ሐ. የማህበሩን አላማዎች ለማስፈጸም የገቢ ምንጮች የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፣
   መ. የማህበሩን ፖሊሲ በማመንጨት ያቀርባል፣
   ሠ. የማህበሩን ጽ/ቤት ይመራል ፣ ይቆጣጠራል፤
   ረ. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣ዝውውር፣ እድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል፡፡
   ሰ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡
   ሸ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል፡፡

ቀ. የአባልነት ግዴታቸውን የልተወጡ አባላት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሐሳብ የቀርባል

በ. የራሱን የአሰራር ስነ ስርዓት ያወጣል፡፡

ተ. በጠቅላላ ጉባዔው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

ቸ. የማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፡፡

## አንቀጽ 19፡ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

1. የሥራ አስፈፃሚ 7 አባላት ይኖሩታል፣
2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. ኘሬዘዳንት

   ለ. ፀሐፊ

   ሐ. አቃቢ ነዋይ

   መ. የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰር

   ሠ. ኘሮግራም ኦፊሰር እና

   ረ. ሌሎች ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡
3. <u>ኘሬዘዳንቱ/ቷ</u>

   በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቋቁማቸውን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን በሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡

   ለ. ማህበሩን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

   ሐ. በማህበሩ ስም የተከፈተውን የባንክ ሒሳብ ቼኮችንና የወጪ ሰነዶችን ከሒሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፡፡

   መ. ለማህበሩ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ያፀድቃል፣

   ሠ. የ 3 ወር የ6ወርና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ራፖርቶችን እያዘጋጀ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

   ረ. በማህበሩ ሥም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

   ሰ. የማህበሩ ጽ/ቤት የዕለት ተዕለት ሥራ መሠራቱን ይከታተላል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል

   ሸ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በማስፈቀድ በማህበሩ ሥም ንበረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ ውሎችን ይዋዋላል፡፡

   ቀ. በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላል፡፡

   በ. ሌሎች በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

4. <u>ፀሐፊው/ዋ</u>

ሀ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል

ለ. ኘሬዝዳንቱን በማይኖርበት ጊዜ ወክሎ ይሠራል

ሐ. ከሥራ አሰፈፃሚ ኮሚቴው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የማህበሩን የመፃፃፍ ግንኙት ሥራዎች ያከውናውናል፡፡

መ. የሥራ አስፈፃማውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

ሠ. የማህበሩን ማህተም፣ ሰነድና መዛግብት በጽ/ቤቱ በጥንቃቄ መያዙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል ለውሳኔ ያቀርባል፤

5. <u>አቃቢ ነዋይ</u>

ሀ. የማኅበሩ ሒሳብ ደብተሮችን፣ የማኅበሩን ከጊዜ ወደጊዜ ያለውን የሒሳብ መረጃዎችን በሙሉ በአግባቡ መጠበቃቸውን ክትትል ያደርጋል፣ይቆጣጠራል፤

ለ. በሁሉም የገንዘብ ዝውውር ሰነዶች ላይ ከኘሬዝዳንቱ ጋር በመሆን ይፈርማል፤

ሐ. በማኅበሩ በጀት ዝግጅት ለይ የመጠባበቂያ ገንዘብንና ሌሎች ወጪዎችን ይቆጣጠራል፤

መ. ከማኅበሩ የውስጥ ኦዲተር ጋር በመሆን የማኅበሩን አመታዊ የሒሳብ መግለጫ ያዘጋጃል፤

ሠ. የማኅበሩ ንብረት በአግባቡ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ይቆጣጠራል፤

ረ. ለማኅበሩ ሒሳብ ትክክለኛ ኦዲት የሚያስፈልጉትን የሒሳብ መረጃዎችን እና መዛግብቶች በተጠየቀ ጊዜ እንዲቀርቡ አመራር ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6. <u>የሕዝብ ግንኙነት ኦፊሰር</u>

ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን

ሀ. የሕፃናት ሐኪሞች የዚህ ማኀበሩ አባል እንዲሆኑ ያበረታታል፤

ለ. የማኅበሩ እንቅስቃሴዎችንና የሥራ አፈፃፀም መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ያሳውቃል ያስረዳል፤

ሐ. የሕትመቶች ስርጭት በአግባቡና በወቅቱ እንዲሰራጭ ያደርጋል፤

መ. የገቢ ማስገኛ ዝግጅቶችን የመዝናኛና የአባላት መገናኛ መድረኮችን ያዘጋጃል፡፡

7. <u>ኘሮግራም ኦፊሰር</u>

ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን

ሀ. ኮንፈረንሶችን፣ ሴሚናሮችን እና ተከታታይ የሕክምና ትምህርት ኘሮግራሞችን ያቅዳል፣ ያደራጃል፤

ለ. የምርምር ስራዎችን እና እትሞቻቸውን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ሐ. ከእነዚህ ስራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዛግብቶች ይጠብቃል፣

## አንቀጽ 20፡ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት የአባላት አገልግሎት ዘመን

1. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ሰብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በኘሬዝዳንቱ ወይም ምክትል ኘሬዝዳንቱ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ ድጋሚ የስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሣኔዎችን በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ኘሬዝዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይፀናል፣
5. የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አንድ የኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም፣
6. የኮሚቴ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለማህበሩ ስራ ለሚያወጡት ወጪ ማካካሻ ይከፈላል፡፡

## አንቀጽ 21፡ የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የማኅበሩ ኦዲተር የማህበሩን ኘሬዝዳንት ወይም የሥራ አሰፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኦዲተር ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

2.1. የማኅበሩ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣

2.2. ማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣

2.3. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፤

## አንቀጽ 22፡ የማህበሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ኃላፊነትና ተግባር

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ፡-

1. የማህበሩን ጽ/ቤትን በበላይነት ይመራል፣
2. የማህበሩ የዕለት ከዕለት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የማህበሩጽ/ቤት ሠራኞችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
4. የማህበሩ ንብረትና ገንዘብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
5. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችንና አመራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል፣አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ሪፖርት ያቀርባል፤

6. ለማህበሩ እድገትና የአሠራር መሻሻል የሚጠቅሙ ደንቦችን፣ የአፈፃፀም ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፤
7. በማህበሩ ኀሬዘዳንት/ሥ/አ/ኮ/ ሲወከል ማህበሩን ወክሎ ከመንገስታዊና ከሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣ የግንኙነቱን ውጤት ሪፖርት ያቀርባል፤
8. የማህበሩን ማህተም ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
9. ሌሎች ክሥ/አ/ኮ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፤

## አንቀጽ 23፡ የማኀበሩ የገቢ ምንጭ

የማኀበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 24፡ የማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት  በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ይሆናል የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ ወይም ኀሬዝዳንት የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስበሰባ ¾ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው፣፣
4. የመተዳደሪየ ደንቡ እነዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ኤጀንሲው ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ምክንያት ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይቀጠራል፡፡
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

## አንቀጽ 25፡ ስለማኀበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. ማህበሩ ወደተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማህበር ጋር የማዋሃደው ወይም ወደ በጎ አድራጎ ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ¾ኛ ድምጽ ሲወሰን ነው፡፡
2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማህበር ጋር የሚደረገው ድርድር የሚያከናወነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ ፣ ፀሀፊና የማህበሩን ኀሬዝዳንት ማካተት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 26፡ ስለማኅበሩ መፍረስ

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ¾ኛ ድምጽ ሲወስኑ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩን ኀሬዝዳንት የንብረት ቆጠራ (inventory) ሰርቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 27፡ የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በበጎ አድራጉት ድርጅቶትና ማህበራች ኤጀንሲ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡